Amharic (አማርኛ)

# ኮሮናቫይረስ (COVID-19): ስለ ኮቪድ/COVID-19 ምን እንደሚታወቅ

## ለኩውንስላንድ ነዋሪዎች መረጃ

### ኮቪድ/COVID-19 ምንድ ነው?

ኮቪድ/COVID-19 ኮሮናቫይረስ የሚፈጠር የበሽታ ብክለት ነው። ኮቪድ/COVID-19 የያዛቸው አብዛኞች ሰዎች መካከለኛ የሆነ ህመም ብቻ እንዳለባቸውና ያልምንም ለየት ያለ ህክምና ያገግማሉ። አንድ ሰው እንዴት እንደሚታመም በተለያየ መልኩ ኮቪድ/COVID-19 ዓይነት በተያያዘው ሰው ይለያያል።

<u>እንዴት ኮቪድ/COVID-19 ይሰራጫል?</u>

ኮቪድ/COVID-19 መስራጨት የሚችለው በሰዎች መካከል የሚተላለፈው የተበከለው ሰው ሲስል፣ ሲያነጥስ፣ ሲናገር ወይም በጣም በሚተነፍስበት ጊዜ በሚወጣ ጥቃቅን ፈሳሽ ነገሮች በኩል ይሆናል።

ኮቪድ/ COVID-19 ካለበት ሰው ሲተነፍስ በቅርበት ግንኙነት ካደረጉ ወይም እሱ የነኩትን የሆነ ነገር በመንካትና ከዚያም የርስዎን ዓይኖች፣ አፍንጫ፣ ወይም አፍ ሲነኩት መበከል ይችላሉ።

እንዴት ኮቪድ/COVID-19 እንደሚሰራጭና እርስዎን እንዳይዝዎ ለመከላከል የበለጠ መረጃ ማግኘት የሚችሉት ድረገጽ: www.qld.gov.au/health/conditions/health-alerts/coronavirus-covid-19/protect-yourself-others/coronavirus-prevention

<u>ኮቪድ/COVID-19 "በተለያየ መልኩ" ምን ማለት ነው?</u>

ኮቪድ/COVID-19 በሚሰራጭበት ጊዜ ልክ እንደ ኢንፍሉዌንዛ ፍሉ ሊቀያየር ይችላል። ይህ ለቫይረስ የተለመደ ነው። እነዚህ ለውጦች "ራሄያዊ/ተቀያያሪ/mutations" ተብሎ ይጠራል። በራሄያዊ ለውጥ ለመጀመሪያው ቫይረስ "የተለያየ መልኩ/variant" ተብሎ ይጠራል። በተለያየ መልኩ ኮቪድ/COVID-19 እንዳሉ፣ በዚህ የሚካተት ደልታ/Delta (ቀደም ሲል *ከህንድ የመነጨ*)፣ አልፋ/Alpha (ከይናይትድ *ኪንግዶም የመነጨ*)፣ በታ/Beta (ከሳውዝ *አፍሪካ የመነጨ*)፣ ጋማ/Gamma (*ከብራዚል የመነጨ*) እና ከዚያ በላይ። የተለያየ ምልክ ያለው ቫይረስ ከሌሎቹ በቀላሉ መስራጨት ሲችል ነገር ግን አሁንም ተመሳሳይ ኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ ነው።

የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት ስለተለያየ መልኩ ኮቪድ/COVID-19 የበለጠ መረጃ ለማግኘት ድረገጽ: www.who.int/en/activities/tracking-SARS-CoV-2-variants/ .

### በአብዛኛው ችግር የሚያጋጥመው

በሁሉም እድሜ ገደብ ወይም ጤና ሁኔታ ላይ ያሉት ሰዎች በኮቪድ/COVID-19 መያዝ ይችላሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች በበለጠ ችግር ላይ እንደሚሆኑና በቫይረስ ከተያዙም በእርግጠኝነት ይታመማሉ። በዚህ የሚካተት:

- በእድሜ አንጋፋ ለሆኑ ሰዎች ።
- በአሁኑ ጊዜ ህመም ላለባቸው ሰዎች፣ እንደ ነቀርሳ፣ የሳንባ ችግሮች፣ የስኳር በሽታ፣ ወይም ከፍተኛ የደም ግፊት ላለባቸው ሰዎች።
- በቡድን መጠለያ ቤቶች ለሚኖሩ ሰዎች።
- በእስር ማረሚያ መገልገያዎች ላሉ ሰዎች።

ለእነዚህ ሰዎች ደህንነት ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ አለብን። በዚህ የሚካተት ማንኛውም የኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች ካለብዎት እነሱን እንዳይነበኙ ማድረግ።



Queensland Government

## የኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች

በኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች ላይ የሚካተት:

- ትኩሳት
- ሳል
- የጉሮሮ ህመም
- የትንፋሽ እጥረት
- እራስ ምታት
- በአፍንጫ ፈሳሽ ወይም መዘጋት
- ከፍተኛ ድካም
- ተቅማጥ፤ ትውከት ወይም ማቅለሽለሽ
- የጣእም ወይም ሽታ ስሜት ማጣት
- የጅማት ወይም መገናኛ ህመም፤ እና
- የምግብ ፍላጎት ማጣት።

ሰዎች የተለያየ ኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች ሊያጋጥማቸው ይችላል። በጣም ከባድ የሆነ ኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች ካሉብዎት፤ ይህ ማለት እስኪ.ያገግሙ ድረስ ረጅም ጊዜ ይወስድብዎታል። ለምሳሌ: በቫይረሱ በጣም ከባድ የበሽታ ምልክቶች ላለባቸው ሰዎች ለማገገም ብዙ ሳምንታት ወይም ወራት ሊወስድባቸው ይችል ይሆናል። መካከለኛ የበሽታ ምልክቶች ያለባቸው ሰዎች ከአንድ እስከ ሁለት ሳምንታት ውስጥ ሊሻላቸው ይችል ይሆናል።

ማንኛውም የኮቪድ/COVID-19 በሽታ ምልክቶች ካለብዎት፤ በተቻለ ፍጥነት ምርመራ ማድረግ አለብዎት። በአቅራቢያዎት ያለን የኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄጃ በዚህ ድረገጽ ማግኘት ይችላሉ: [www.qld.gov.au/health/conditions/health-alerts/coronavirus-covid-19/stay-informed/testing-and-fever-clinics.](www.qld.gov.au/health/conditions/health-alerts/coronavirus-covid-19/stay-informed/testing-and-fever-clinics)

**የሚቀርብ ድጋፍ**

ኮቪድ/COVID-19 ሁኔታን ለመቋቋም ችግር ከሆነብዎት፤ ለመድብለ ባህላዊ መገናኛ በስልክ 1300 079 020 መደወል። በቋንቋ እርዳታ ከፈለጉ አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎት መጠየቅ።

ስለ ኮቪድ/COVID-19 ህዝባዊ ጤና ጥበቃ መመሪያዎች፤ ማንኛውም ጥያቄ ካለ ለህዝባዊ ጤና ጥበቃ በስልክ 134 COVID (**13 42 68**) መደወል። ምን እንደሚደረግ ይነግርዎታል። አስተርጓሚ ካስፈለግዎት፤ በሚደውሉበት ጊዜ መጠየቅ። ይህ በነጻ ነው።